Email: contact@shegasab.com
Land line: +251 115 57 97 57
Mobile: +251 980 37 38 39

Turning Inspirations into Income

Shegasab

Shegasab Training and Consultancy PLC

## አካባቢያዊ ምልከታ መብቶች (Geographical Indications)

ከንግድ ምልክቶች ጋር በተያያዘ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ የአካባቢያዊ ምልከታ መብቶች ይጠቀሳሉ። የአካቢያዊ ምልከታ መብቶች እንደ ንግድ ምልክቶች ሁሉ ምልክቶች (Marks) ሲሆኑ የሚለያቸው ነገር የአካባቢያዊ ምልከታ መብቶች ከስማቸው እንደምንረዳው ስያሜዎቻቸውን የሚያገኙት ምርቱ ከሚፈልቅበት አካባቢ ነው። ይህ ማለት የአካባቢ ምልከታ መብቶች የምርቱን የተለየ ጣእም ወይም ጥራት ከሚገኝበት አካባቢ ተፈጥሯዊ ሁነቶች ጋር የተሳሰረ ሲሆን የሚሰጥ ነው።

በተጨማሪም ምርቱ በብቸኝነት የሚገኘው በአንድ ውስን አካባቢ ብቻ ከሆነ ይህን መብት ሊያገኝ ይችላል።

ለምሳሌ በሃገራችን የኢትዮጵያ ቡና ወይም ሌሎች ሃገር በቀል የሆኑ ምርቶችን ወይም በጣእም ወይም በጥራታቸው የአንድ አካባቢ ተጽእኖ ያለባቸው ምርቶች፤ በአለም አቀፍ ደረጃም ከፈረንሳይ የሚመጣው ሻምፓኝ መጠጥ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ (ሻምፓኝ በፈረንሳይ የሚገኝ ቦታ ስም ነው)።

ይሁን እና እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት እና መሰል ሀብቶች በአካቢያዊ ምልከታ ወይስ በጋራ የንግድ ምልክት ይጠበቁ? የትኛው መንገድ የተሻለ ነው የሚለው አልፎ አልፎ ሲያከራክር እንመለከታለን።

በመሰረቱ አካባቢያዊ ምልከታ መብትን የምንጠቀም ከሆነ በአንድ ውስን አካባቢ ያለን ተፈጥሮ ተንተርሶ የሚመጣን ልዩ ምርት መሆን አለበት። ይህ ደግሞ የዚህን መብት አጠቃቀም ላይ እክል ይፈጥራል። ለምሳሌ የቡና ምርትን ብንወስድ እንደ እኛ ሃገር ባሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አርሷደሮች በትናንሽ መሬቶች ላይ የሚያበቅሉት ሰለሆነ ከአካቢያዊ ምልከታ ይልቅ የጋራ የንግድ ምልክቶች የተሻለ መብትን ሊያገኙ ይችላሉ።

ኢትዮጵያ ምንም እንኳ የአካባቢያዊ ምልከታ መብት ባታጸድቅም እነዚህን መብቶች ለማስጠበቅ አማራጭ መንገዶችን ትጠቀማለች። በተመሳሳይ ሰሜን አሜሪካ የአካባቢ ምልከታ መብት ቢኖራትም በአመዛኙ ግን የምትጠቀመው የጋራ የንግድ ምልክቶች እና የማረጋገጫ ምልክቶችን (Certification Marks) ነው።

የጋራ የንግድ ምልክቶች የምርቱን እና የአካባቢው ትስስር የማይፈልጉ መሆናቸውም በጥበቃቸው ላይ የተሻሉ ያደርጋቸዋል። ይህም ማለት ምርቱ ቦታ ቀይሮ ቢመረት ወይም ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ቢሰፋ ጥራቱን እስከጠበቀ እና የጋራ ምልክቱ አባል እስከሆነ ድረስ ብራንዱን መጠቀም ይችላል።

*ጥያቄ ካለዎት ወይም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ በየሳምንቱ የነጻ ጥያቄ እና መለስ ፕሮግራማችንን ወይም በትሬኒንግ ውስጥ ከተዘረዘሩ ስልጠናዎች መካከል መርጠው ይመዝገቡ። ወይም ኮንታክትን በመንካት ያግኙን!*

© [2025] Shegasab. All Rights Reserved. The unauthorized reproduction, distribution, or transmission of this text is strictly prohibited and subject to legal action under applicable copyright law.